# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 97 መጋቢት 16 2002 ዓ.ም


**ምርጫን እንደመሰለያ መሳሪያ የሚጠቀመው ወያኔ በድህረ ምርጫ 97 በህዝባችን ላይ የፈጸመው አይነት ፋሽስታዊ ጭፍጨፋ እንዳይደገም ከተፈለገ፣ ነጻ እና ገለልተኛ የሆነ የምርጫ አስፈጻሚ አካላት፤ ለሁሉም እኩል የሚያገለግል የሚዲያ አገልግሎት፤ ታማኝነታቸው ለህገመንግሥቱ ብቻ የሆነና ከፖለቲካ ወገናዊነት የጸዱ የፖሊስ፤ የመከላኪያና የደህንነት ተቋማት መመስረት ይኖርበታል።**

**ለወያኔ እድሜ መራዘሚያ ህጋዊና ሞራላዊ መሰረት እንዲያስገኝ ታስቦ በሚካሄድ ምርጫ መሳተፍ ለህዝባችን የሚያስገኘው ፋይዳ አይኖርም!!!**

## አምባገነኑ መለስ ዜናዊ ከምርጫው በኋላ ለፍርድ የሚቀርቡ ይኖራሉ ሲል መዛቱ ተሰማ

በአምባገነንነቱና በዘረኝነቱ የሚታወቀው መለስ ዜናው አሻንጉሊት በሆነው የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ስብሰባ ላይ እንዳስታወቀው በቀጣዩ ምርጫ ከመጫወቻ ሜዳው ወጥተው በህግ ጥሰት ላይ ተሰማርተዋል ያላቸውን ፓርቲዎች መንግስት ክስ ሊመሰርትባቸው እንደሚችል በመዛት አስታውቋል። እንደመለስ አገላለጽ የምርጫውን ሂደት ለማደናቀፍ እየሰሩ የሚገኙ ሃይሎች በተለያየ ደረጃ የሚታዩ መሆናቸውን፣ ይህን አደናቃፊ ስራ የሚሰሩ ሃይሎች ደግሞ ሆን ብለው አቅደው ከተነሱት የታጠቁት ሃይሎች ጀምሮ አውቀውም ሆነ ሳያውቁ ስህተቱን የሚፈጽሙ ህጋዊ እውቅና ያላቸውን የፖለቲካ ሃይሎችም የሚጨምር መሆኑን በይፋ ተናግሯል። ህጋዊ እውቅና ኖሮአቸው ህገወጥ ስራ እያከናወኑ ይገኛሉ ባላቸው የፖለቲካ ሃይሎች ላይ ስለሚወሰደው ርምጃ ሲናገር ከመጫወቻው ሜዳ ወጥተው ባጉራ ዘለልነት ህግ እየጣሱ የሚገኙት በማለት የተለመደ የዘለፋ ንግግሩን ያደረገው መለስ ባሁኑ ሰአት በነኝህ አጉራ ዘለሎች ላይ እርምጃ ለመውሰድ መሞከር ሰዶ ማሳደድ ይሆንና ምርጫውን ያውከዋል ብሏል። በመቀጠልም አገዛዙ ምርጫው ከተጠናቀቀ በኋላ በሚሰበሰብ ማስረጃ ላይ ተመስርቶ ህጋዊ ርምጃ መውሰድ የመጨረሻው ይሆናል በማለት ዝቷል።

**(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)**

## የቀድሞው የባንድ ኤይድ ዳይሬክተር ህወሀት የርዳታን ገንዘብ ለጦር መሳሪያ ግዢ ማዋሉን አረጋገጡ

ደይሊ ሜይል የመረጃ ድረ ገጽ ባወጣው ጽሁፍ ቦብ ጊልዶፍ ቀደም ብሎ በቢቢሲ ሪፖርተር የቀረበውን ዘገባ ማጣጣሉንና መረጃ ከተገኘ ግን ይህን መንግስት እፋረዳለሁ ማለቱን አውስቶ፣ በወቅቱ የባንድ ኤይድ ዳይሬክተር በመሆን ኢትዮጵያ ውስጥ እንደፈረንጆች አቆጣጠር ከ1985-91 ባለው ጊዜ ውስጥ ሲሰሩ የነበሩትን የ85 ዓመቱን ጆህን ጄምስ በመጥቀስ በርግጥም ከርዳታው ገንዘብ ውስጥ ቢያንስ 20 በመቶ የሚሆነው ለጦር መሳሪአያ ግዢ መዋሉን ማረጋገጣቸውን ይፋ አድርጓል።

ጆህን ጄምስ በዚሁ የእማኝነት ቃላቸው ቀደም ብሎ እነአረጋዊ በርሄ ከርዳታው ገንዘብ ውስጥ የተወሰነ ለጦር ግዢ እንደዋለ ማጋለጣቸውን የሚስማሙበት መሆኑን አስረድተው በተገለጸው የገንዘብ መጠን ግን ተጋንኖ ሊሆን ይችላል ብለዋል፡፡ ጆህን ጄምስ እንደተናገሩት ማንም አካል በወቅቱ ለርዳታ ከተሰበሰበው ገንዘብ ውስጥ ምንም ሳንቲም ለጦር መሳሪያ ግዢ አልዋለም ብሎ ለመከራከር መሞከር ከንቱ ድካም እንደሆነ አስረድተው ይህም ድርጊት እንደሳቸው ግምት በወቅቱ ርዳታውን ባደረጉ ድርጂቶች ሁሉ የሚታወቅና ተቀባይነት ያገኘም እንደነበር ጠቅሰዋል፡፡ **(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)**

## የአማራ ክልል አስተያየት ሰጪዎች ወያኔ የሃገሪቱን ሉአላዊነት አስከብራለሁ ማለቱ ንቀት ነው አሉ

"ለሁለት አስርተ ዓመታት የስልጣን ወንበሩን የሙጥኝ በማለት የኢትዮጵያን ህዝብ ወደደም ጠላም እንደፈለግሁ ረግጬ እገዛዋለሁ" በሚል ከንቱ ቅዠት ውስጥ የተዘፈቀው የወያኔው አገዛዝ፣ "ከመረጣቺሁኝ የሃገሪቱን ሉአላዊነት አስከብራለሁ ማለቱ እጂግ በጣም አሳፋሪና ለኢትዮጵያ ህዝብም ያለውን ንቀት አጉልቶ የሚያሳይ" መሆኑን የግንቦት ሰባት ዘጋቢ ያነጋገራቸው አንዳንድ የደብረ ማርቆስ ነዋሪዎች ገለጸዋል። አንድ በንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ አስተያየት ሰጪ ለዘጋቢያቹን በሰጡት አስተያየት የወያኔ ልፍለፋና ጆሮ ማደንቆር ለርሳቸው አዲስ አለመሆኑን ገልጸው፣ በዚሁ በያዝነው ወር እየተደረገ ባለው የምረጡኝ ክርክር ተብየ ቀደም ብሎ የአማራ ክልል ከፍተኛ ባለስልጣን የነበረውና ከዚያም በኋላ በትምህርት ሚንስትርነት ተሹሞ የሚገኘው ደመቀ መኮነን ህዝቡ ወያኔን ከመረጠ የሃገሪቱን ሉአላዊነት እናስከብራለን ብሎ መናገሩ እጂግ እንዳስገረማቸው ብሎም እንዳሳዘናቸው ገልጸዋል። ደመቀ መኮነን የአማራ ክልል ዋና ጸሀፊ በነበረበት ወቅት በሱዳን አዋሳኝ የሚገኘውን ከ30 ኪ.ሜ በላይ ስፋትና ከ1600 ኪ.ሜ በላይ ርዝመት ያለውን ሰፊ ለም መሬት የዓማራን ክልል ህዝብ ከምንም ሳይቆጥር ከሱዳን ጋር ተፈራርሞ አሳልፎ እንዲሰጥ ማድረጉ ሳያንስ፣ አሁንም ባደባባይ ለኢትዮጵያ ዳር ድንበር መከበር በጽናት እንቆማለን ብሎ መናገሩ ለህዝብ ያለውን ንቀት ብቻ ሳይሆን ጭራሽ **(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)**

**ግዜ** ግንቦት 7 ዜና

## ወያኔ አዳዲስ የጦር መሳሪያዎችን ወደ ሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ እየላከ መሆኑ ታወቀ

አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ ሰላማዊና ፍትሃዊ የሆነ ምርጫ ለማካሄድ ዝግጅቴን ጨርሻለሁ እያለ በሚናገርበት ባሁኑ ሰዓት አዳዲስ የጦር መሳሪያዎችን ወደ ሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ እየጫነ መሆኑን የደህንነት ምንጮቻችን ገለጹ። ምንጮቻችን እንደገለጹት ወያኔ መጋቢት 4 ቀን 2002 ዓ.ም ደማቅ አረንጓዴ ቀለም ባላቸው 8 ቮልቮ ተሳቢ የጦር ካሚዮኖች 16 ኮንቴይነር የጦር መሳሪያ ወደሁመራ አቅጣጫ ማጓጓዙ ታወቋል። በነኚሁ ከ16 በላይ የሚሆኑ አዳዲስ ኮንቴይነሮች ተጪኖ ወደ ሰሜን ምእራብ የተላከው የጦር መሳሪያ ፒ.ኬ.ኤም. ከባድ መትረጌስ በደገኑ ሁለት ፒክ አፕ ቶዮታ ወታደራዊ ፈጣን መኪኖችና የጦር መሪዎችም የታጀበ መሆኑን ምንጮቻችን ገልጸዋል። ባሁኑ ሰአት የታየው ይህ የጦር መሳሪያና ወታደራዊ ቁሳቁስ የማጓጓዝ ተግባር ከየካቲት 23 እስከ 28 ቀን 2002 ዓም በባህር ዳር ከተማ ከተደረገው የጦር መኮንኖች ስብሰባና በስብሰባውም ከተወሰዱ ውሳኔዎች ጋር የተያያዘ መሆኑን እነኚሁ ምንጮቻችን አክለው ገልጸዋል። **(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)**

## የወ/ት ብርቱካን ሚዴቅሳ የጤና ሁኔታ አሳሳቢ ሆኗል ተባለ

በአረመኔአዊው የወያኔው አገዛዝ በቃሊቲ ወህኒ ቤት በግፍ ታስራ የምትገኘው የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ሊቀመን በር ወ/ት ብርቱካና ሚደቅሳ ህክምና በመከልከሏ የጤንነቷ ሁኔታ አሳሳቢ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ከወህኒ ቤቱ አካባቢ ከተገኙ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡ ህመሟ ከወህኒ ቤቱ ክሊኒክ አቅም በላይ በመሆኑ ለአንድ ግዜ ወደ ሆስፒታል መላኳን የገለጹት የመረጃ ምንጮች፣ ህክምና ያደረገላት ሀኪም ተጨማሪ ህክምና እንደሚስፈልጋትና በሌላ ሐኪም መታየት እንደሚገባት የገለጸ ቢሆንም ወህኒ ቤቱ ይህን ተግባራዊ ባለማድረጉና ህክምናም እንዳታገኝ ጭራሹኑ በመከልከሉ የጤናዋ ሁኔታ እለት ከእለት እየባሰ መምጣቱን ለመመልከት መቻላቸውን ገልጸዋል፡፡

በአረመኔያዊነቱና በጨካኝነቱ የሚታወቀው መለስ ዜናዊ ስለ ወ/ት ብርቱካን የጤና ሁኔታ ተጠይቆ በሰጠው መልስ "ትንሽ ክብደት ከመጨመሯ በስተቀር በጣም ደህና ነች ቤተሰቦቿም ይጠይቋታል" በማለት የሰጠው መልስ በጣም አሳዝኖናል ያሉት የመረጃ ምንጮች፣ ይህን መረጃ ለመስጠት ያስገደዳቸውም የመለስ ንግግርና መጋቢት 12/2002 በብርቱካን ላይ የተመለከቱት አሳዛኝ ሁኔታ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ **(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)**

## በርካታ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ውሀ ካዩ አምስተኛ ቀናትን ማሳለፋቸውን ገለጹ

በአዲስ አበባ ከተማ የተለያዩ ክፍለ ከተሞች በደረሰው የውሃ አቅርቦት እጥረት ምክንያት በርካታው የህብረተሰብ ክፍል ለአለፉት አምስት ቀናት በከፍተኛ ሁኔታ እየተሰቃየ መሆኑ ተገለጸ። አዲስ አበባ የሚገኘው የግንቦት ሰባት ዜና ዘጋቢ በተለያዩ ክፍለ ከተሞች ተዘዋውሮ አንዳንድ ነዋሪዎችን ያነጋገረና የተፈጠረውን የውሃ አቅርቦት እጥረትም በቅርብ የታዘበ ከመሆኑም በላይ ይህ የውሃ እጥረት ከተከሰተ አምስተኛ ቀኑን እያስቆጠረ እንደሆነም ገልጿል። ከዚሁ ጋር በማያያዝ ዘጋቢያችን እንደገለጻልን በርካታ የሆኑ በተለይም በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ በእድሜ የገፉ አዛውንትን ጨምሮ በርካታ የሚሆኑ ነዋሪዎች ለእለት ፍጆታቸው የሚሆነውን ውሃ ለማግኘት ረጂም **(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)**

## ሂዩማን ራይትስ ወች በኢትዮጵያ ያለው የፖለቲካ ሁኔታ እጂግ አሳሳቢ መሆኑን ገለጸ

ሂዩማን ራይትስ ዎች በኢትዮጵያ ላለው ሃሳብን በነጻነት የመግለጽና የመደራጀት መብት ጥሰት "አንድ መቶ ጫና መፍጠሪያ መገዶች" በሚል ርእስ ባወጣው 64 ገጽ ጽሁፉ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ስላለው የሰብአዊ መብቶች ጥሰት በስፋትና በጥልቀት በመዳሰስ የአሜሪካን፤ የካናዳ፤ የኖርዎይ፤ የአውሮፓ ዩኒየን አባል ሃገራት እንዲሁም የዓለም ባንክ ሊወስዷቸው ስለሚገቡ ርምጃዎች ዝርዝር ሀሳቦችን አቅርቧል።

ሂይማን ራይትስ ወች በዚሁ ጽሁፉ ባወጣው መግለጫ በኢትዮጵያ ቀደም ብሎ በተካሄደው የ1997ቱ ምርጫ ማግስት የበርካታ ንጹሃን ዜጎች ደም መፍሰሱን፤ እጂግ በርካታ የሚሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ በጸጥታ ሃይሎች ከፉኛ መንገላታቱን፤ ከ30 ሺህ ህዝብ በላይ ወደ እስር ቤት እንዲገባ መደረጉን አውስቶ፤ ባለፉት 5 ዓመታት የሃገሪቱ መንግስት የፖለቲካ ምህዳሩን ከጊዜ ወደ ጊዜ እጂግ እያጠበበ መምጣቱን፤ የዜጎችን በነጻነት የመንቀሳቀስና ከነጻ የዜና አውታሮች መረጃ የማግኘት መብቱንም በእጂጉ መጣሱን፣ በተለይም ብርቱካን ሚዴቅሳን በመጥቀስ የተቃዋሚ ፓርቲዎች አባላትና ደጋፊዎች በጂጉ መዋከባቸውንና ለእስር መዳረጋቸውን፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ **(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)**

## ሥነ-ምግባር ደህና ሰንብት

ሰሞኑን መለስ ዜናዊ "ተቃዋሚዎች በምርጫ ክርክር ወቅት የሚናገሩትን እንቀዳና ከምርጫ በኋላ በማስረጃነት ተጠቅመን እንከሳቸዋለን" በማለት በፓርላማ ውስጥ ያደረገውን ንግግር የምርጫ አፈፃፀም ሥነ-ምግባር ደንብን የጣሰ ስለመሆኑ ደንቡን የፈረሙ ፓርቲዎች አመራሮች መግለጫ ሰጥተውበታል።

በእኛ እምነት የመለስ ዜናዊ ከላይ የተጠቀሰው ንግግርና ሌሎቹም የሰሞኑ መግለጫዎቹ በጥቅሉ ሲታዩ የጣሱት አንድ የምርጫ አፈፃፀም ሥነ-ምግባር ደንብን ሳይሆን ባጠቃላይ ሥነ-ምግባርን ነው። እንዲህ ዓይነት ንግግሮችን ከአዕምሮ ህመምተኛ አሊያም አንዳችም የሥነ-ምግባር ለከት ከሌለው ወራዳ ብቻ ነው መጠበቅ የሚቻለው። ሰሞኑን ከመለስ አንደበት ከተሰሙ በርካታ አሳፋሪ ንግሮች አራቱን ብቻ ነቅሰን እናውጣ።

1. **"አሁን የምትናገሩትን ቀድተን በኋላ እንከሳችኋለን" ያለውን በተመለከተ፤**

   አንድ ራሱን መንግሥት ነኝ ብሎ የሚጠራ ተቋም ቁንጮ ራሱ ባወጣው ህግና በራሱ ዳኝነት እየተፎካከሩት ያሉትን ሰዎች "አሁን እንዳሻችሁ ተናገሩ፤ በኋላ አሁን በተናገራችሁት መነሻነት እከሳችኋለሁ" ሲል መስማት ይዘገንናል። ይህ ሳጥናዔላዊ ስልት ከሰው አንደበት መውጣቱ የሰውን ልጆች በሙሉ የሚያሳፍር ነው። ደግነቱ እነዚህ ቃላት የወጡት ስብዕናውን ካጣው ከመለስ ዜናዊ መሆኑ ነው።

   አገራችን ስብዕናውን ለሥልጣንና ለአፍቅሮተ ንዋይ በሸጠው እና በዚህም ሳቢያ ጭንቅላቱ ክፉኛ በታመመ ሰው መዳፍ ውስጥ ነች። ራስን ለመከላከል ባይጠቅሙም ፓርላማ ተብየው ሲያል ውስጥ ይህንን ሰይጣናዊ ስልት በገዛ ጆሮዎቻቸው የሰሙ ሰዎች የሚከተሉት ጥያቄዎችን እንዲጠይቁ እንመክራለን። ለመሆኑ ከምርጫው በኋላ የሚያስከስሰው ነገር ምን እንደሆነ ተለይቶ ይታወቃል? ሰውን "ጭቃ፣ ገለባ፣ ዝቃጭ" ብሎ መስደብ ያስቀጣል? አረና ትግራይን ለማጥላላት ሲባል ከጠላቶቻቸን ጋር ያበሩ በማለት አማራና ኦሮሞን የትግራይ ሕዝብ ጠላት እንደሆኑ አድርጎ መቀስቀስስ ያስቀጣል?

   በምርጫ 97 ማግሥት የቅንጅት መሪዎች ለተከሰሱባቸው ወንጀሎች ማስረጃ ናቸው ተብለው በቀረቡ የቪዲዮ ምስሎች ውስጥ ዋነኞቹ ተናጋሪዎች ያኔም ፓርላማ ውስጥ ተኮፍሰው ነበር፤ አሁንም እዚያው ናቸው። ዘንድሮስ እነማን በተናገሩት እነማን እንደሚከሰሱ ተለይቷል?

2. **"ስማችን መጥፋቱ የለመድነው ነው" የተባለውን በተመለከተ፤**

   በ1970ዎቹ የችጋር ወቅት በረሃብ ለተጎዱ ወገሮቻችን የተላከውን ገንዘብ ለመዝረፍ ሲሉ መለስና ጓደኞቹ አሸዋዎችን በጆንያዎች ሞልተው እህል ከላይ በተን አድርገውባቸው ለእርዳታ ድርጅቶች መቸብቸባቸው እና ገንዘቡም ለጦር መሣሪያ ግዢ ከፊሉን ደግሞ ለግል ጥቅማቸው ማዋላቸው ቢቢሲ ማጋለጡ ይታወቃል። ይህንን የቢቢሲ ዘገባ ለማስተባበል መለስና ባልደረቦቹ ያላደረጉት ጥረት የለም። ግን እስካሁን አልሆነላቸውም። እንዲያውም "እኔንም በእማኝነት ቁጠሩኝ" የሚሉ ተጨማሪ ሰዎች እየመጡ ነው።

   ሰሞኑን መለስ ቢቢሲን በስም ማጥፋት ሊከስ ተዘጋጅቶ እንደሆነ ተጠይቆ የሰጠው የትዕቢት ምላሽ "እኛ እንደሆነ ስማችን መጥፋቱ የለመድነው ነው" የሚል ነበር። ይህ ምን ዓይነት ምላሽ ነው? በእውነቱ የዚህን አባባል ትክክለኛ ትርጉም መረዳት ከባድ ነው።ስማቸው መጥፋቱን የለመዱት ከሆነ መሻሻል እንደማይችሉ ተቀብለውታል ማለት ነው? ስማቸው መጥፋቱ የለመዱት ከሆነ ስለ "መልካም ገጽታ" የሚደሰኩሩብን ለምንድነው? ይህ አባባል በውስጡ በስርቆት "ጥበብ" የመኩራራት ድምፀት እና "አርገነዋል ምን ትሆኑ?" የሚል ትዕቢት አለበት።

3. **የአሜሪካ ሬድዮ የአማርኛ ስርጭትን ማፈንን በተመለከተ፤**

   የአንድ አገር መሪ ነኝ ባይ በግልጽ ሬድዮ አፍናለሁ ብሎ በኩራት ሲናገር መለስ የመጀመሪያው ሰው መሆን አለበት። ዝርዝር ጉዳይ ውስጥ ሳንገባ የሬድዮ ሞገድ ማፈን መቻል የአቅም ግንባታ አካል እና የእድገት አመላካች ተደርጎ መቅረቡ የለየት የእብደት ምልክት ነው። ሌላው የአዕምሮ ሕመምተኛ ከሳምንት በፊት "የኢትዮጵያ ህገ-መንግሥት ስለማይፈቅድ ሬድዮ ማፈን አይቻልም" ብሎ ነበር። በዚህ አባባል መሠረት ደግሞ ህገመንግሥቱ ምትሃታዊ የሆነ ፀረ-ሬድዮ-አፈና ኃይል እንደሚያመነጭ ዓይነት ነበር የተገለፀው። እኚህ ሁለቱ ሰዎች የአንድ ቡድን አባላትና የሚያወሩትም ስለ አንድ ጭብጥ መሆኑ ወያኔ አዕምሮዓቸው የተነካ ሰዎች ስብስብ መሆኑን ግልጽ ያደርግልናል።

   ይህ ሁሉ የሚደረገው ህፃናት በረሃብ እየሞቱ እድገትን ወያኔ እንደግል ሃብቱ በሚቆጣጠረው ቴሌቪዥንና በወያኔ ቱጃሮች ፎቆች በሚለኩባት አገር መሆኑ ጉዳዩን ይበልጥ አሳዛኝ ያደርገዋል።

4. **ስለ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን የተናገረውን በተመለከተ፤**

   ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ በግፍ የታሰረች የፓለቲካ እስረኛ ስለመሆኗ የአሜሪካ መንግሥት የሰብዓዊ መብት አያያዝ ሪፖርት እና ሌሎችም በርካታ መንግሥታዊም መንግሥታዊ ያልሆኑም ተቋማት መግለጫዎችን አውጥተዋል። ወ/ት ብርቱካን ብቻዋን ታስራ በደረሰባት ሰቆቃ ምክንያት የጤንነቷ ጉዳይ አሳሳቢ መሆኑን መገለጹን አስመልክቶ ለተጠየቀው ጥያቄ ሲመልስ "ክብደቷ ትንሽ ጨምሯል" ሲል መሳለቁን ምን ይሉታል? ተራ ዋሾ "ታማለች የተባለው ውሸት ነው፤ ጤነኛ ነች" ብሎ ይቆማል። መለስ ግን በጥቂት ተጨማሪ ቃላት ተደራራቢና አሻሚ መልዕክቶችን በመሰንቀር ውሸቱን የውሸቶች ሁሉ የበላይ ያደርገዋል። "ክብደቷ ጨምሯል" ሲል እስር ቤት የቀለብ ችግር የለም፤ እሷ ደግሞ በስንፍናዋ ምክንያት እንቅስቃሴ አታደርግም በማለት የመጀመሪያው ውሸት በብዙ እጥፍ አሳደገው። ይህ ለልማደኛ የመንደር ዋሾ እንኳን ዋጋ የሌለው ጉዳይ ነው። መለስ ለተሸከመው ዓይነቱ ታማሚ ጭንቅላት ግን ታላቅ የደስታ ምንጭ ነው።

መለስ ዜናዊ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የሚሰጣቸው መግለጫዎች ሰውየው ወደ ሙሉ እብደት እያመራ መሆኑን የሚያሳዩ ናቸው።

በሰላማዊ መንገድ እንታገላለን ብለው ወደ ምርጫ የገቡ ድርጅቶችም ከአሁን በኋላ ስለ የምርጫ አፈፃፀም ሥነ ምግባር ደንብ ባያነሱ ይሻላል። መሠረታዊ የሆነ የአነጋገር እንኳን ሥነ ምግባር ባልተከበረበት ሁኔታ የምርጫ አፈፃፀም ሥነ ምግባር ይከበራል ማለት ዘበት ነው።

አገራችን ኢትዮጵያ በእንዲህ ዓይነት ወራዳ ሰው መዳፍ ውስጥ መውደቋ የእኛ ጥፋት ነው። ይህን ሰው ከነግሳንግሱ ማስወገድ የኛ ሥራ ነው። ጊዜ የለም!!! መለስ በስልጣን ላይ የሚቆይበት እያንዳንዱ ተጨማሪ ቀን ለኢትዮጵያ ከፍተኛ ኪሳራ በመሆኑ ተባብረን እንነሳ!

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ**

## አምባገነኑ መለስ ዜናዊ ከምርጫው በኋላ ለፍርድ . . . ከገጽ 1 የዞረ

ይህን የመለስ ንግግር አስመልክቶ ት የአዲስ አበባው የግንቦት ሰባት ዘጋቢ ያነጋገራቸው አንዳንድ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች በሰጡት አስተያየት እንዲህ አይነት ተራና የዘለፋ ቃላት የተካተቱበት ንግግር ከመለስ አፍ መስማት አዲስ አለመሆኑን፤ ይህም ንግግሩ በፓርላማ ተብየው ስብሰባ በይፋ ይነገር እንጂ በተግባር እየዋለ ያለ ከሆነ ቆየት ማለቱን ገልጸው፣ የዚህ ሁሉ ተግባሩ ዋናው ዓላማ ይህን ምርጫ ህዝብንና ተቃዋሚዎቹን ካሁኑ ፍርሃት ውስጥ በመክተት አገዛዙን ብቻ እንደ አማራጭ በማየት እንዲመርጡት ለማድረግ ነው ብለዋል ። በመቀጠልም እኒሁ አስተያየት ሰጪዎች የሚገርመው ነገር ወያኔ ምርጫውን ከወዲሁ ማሸነፉን በተደጋጋሚ እየነገረን ባለበት ሁኔታ የተቃዋሚ ፓርቲዎች እዚህ ፉክክር ውስጥ እናሸንፋለን የሚል ተስፋ መሰነቃቸው ነው ሲሉ ተቃዋሚዎችንም ለመተቸት እንደሞከሩ ገልጿል፡፡

በተያያዘ ዜናም ይህው አምባገነን መሪ የአሜሪካንንና የሌሎችንም የራዲዮ ማሰራጫዎች ማፈን መጀመሩንና የአፈናውም ስራ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ለማድረግ ትእዛዝ እንደሚሰጥ አስታውቋል። መለስ ዜናዊ የሚመለከታቸው ባለስልጣናቱ የአፈና አቅም እንዲያጎለብቱ መመሪያዎች መስጠቱን ያንንም ወደማሳካቱ እየተጠጉ እንደሆነ መረዳቱንና ከዚህም አንጻር ከቅርብ ጊዚያት ወዲህ ሙከራው ተደርጎ ሊሆን እንደሚችል በይፋ ተናግሯል፡፡ ባለስልጣኖቼ ያ የማፈን አቅም እንዳለን ካረጋገጡልኝ ግን ስርጨቱን እንዲያፍኑ ቀጥተኛ ት እዛዝ እሰጣለሁ ሲል ትእቢት በተሞላበት ሁኔታ ተናግሯል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ የቪኦኤው ዳይሬክቶር ዳንፎርት አውስቲን በሰጡት መግለጫ የአሜሪካ ድምጽ የአማርኛ ዜና አገልግሎት የሚሰጠው መረጃና ዘገባ ትክክለኛ ወገናዊነት የሌለውና አጠቃላይ እንዲሆንና ከፍተኛም የጋዜጠኝነት ደረጃ እንዲገዛ በህግ እንደሚጠበቅበት አስረድተው ባለፉት አራትና ከዚያ በላይ ሳምንታት የቪኦኤ አማርኛ ስርጪት እየታፈነ እንደሆነ አድማጮች መግለጻቸውን አውስተዋል። አውስቲን የወያኔው አገዛዝ የቪኦኤን ፕሮግራሞች ከሩዋንዳው ሬዲዮ ጋር ማወዳደሩ ፍጹም የሆነ ስህተትና አሳዛኝም እንደሆነ በአንክሮ መግለጻቸውን የአሜሪካ ድምጽ ዘግቧል።

ይህን የቪኦኤ ዘገባ ተከትሎ በርካታ የመረጃ ድረገጾች በስፋት ሽፋን የሰጡት ሲሆን ቢቢሲ፤ ሬዲዮ ስርቫይቨር፤ ደይሊ ሜይልና ለሎቹም ባወጧቸው ጽሁፎች ቀደም ብሎ በአሜሪካ ድምጽ ዜና እወጃ የአማርኛው ክፍል ስርጪቱ እየታፈነ እንደነበር ሪፖርት መቅረቡን ነገር ግን ስርጪቱን እያፈነ ያለውን አካል ማወቅ ያልቻሉ መሆኑን ገልጸው እንደነበር አውስተው ከዚህ አፈና በስተጀርባ የአገዛዙ እጂ እንዳለበት መረጋገጡን አስፍረዋል፡፡ እነኚሁ ድረገጾች ባወጧቸው ዘገባዎች በተለያዩ ጊዚያቶች አገዛዙ ለሚቀርቡበት ክሶች የሰጣቸውን ማስተባበያዎች ማለትም በሃገሪቱ ውስጥ የፕሬስ አፈና መካሄዱ ውሸት ነው ማለቱን፣ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ወከባ በፍጹም የለም ማለቱን፤ አሁን በቅርብ ጊዜ በቢቢሲ የዜና አገልግሎት የተጋለጠውን ለርሃብተኞች የተሰጥን ገንዘብ ለጦር መሳሪያ ማዋሉንም ማስተባበሉን ጨምረው አውስተዋል፡፡

የወያኔው አፈቀላጤ የሆነው ሽመልስ ከማል ሰሞኑን የኢትዮጵያ ህገመንግሰት አፈናን የሚከለክል በመሆኑ መንግስታችን አፈና ያደርጋል የሚለው መሰረተ ቢስ ውንጀላ ነው ሲል መናገሩ ይታወሳል። የግንቦት7 ራዲዮ አፈና ከተደረገባቸው የራዲዮ ጣቢያዎች መካከል አንዱ መሆኑን መጥቀሳችን ይታወሳል።

በግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን

የፖስታሳጥን ቁጥር ፡- POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

ሃይለ ሀሳብ



# ውጭ ጉዳይ ሲገለጥ

ክፍል 3 ካለፈው የቀጠለ

ከሰራተኛ እድገትና ቅጥር ጋር ተያይዞ መነሳት የሚገባዉ ጉዳይ ደግሞ የትምህርት መረጃ ነዉ።ከውጭ አገር የሚገኝ ማንኛዉም የት/ርት ማስረጃ በኢትዮጵያ ት/ት ሚኒስቴር የአቻ ግምት ይሰጠዋል። በዚህ መሰረት ከውጭ አገር የተገኘ ማስትሬት ዲግሪ አገር ውስጥ ከሚሰጠዉ ማስትሬት ዲግሪ ጋር አቻ ግምት እንዲሰጠዉ ከመጀመሪያ ዲግሪ በሗላ የተገኘ መሆን ይኖርበታል። ይህ ግን ለታጋዮቹ የሚሰራ ህግ አይደለም።እነዚህ ሰዎች ከአገረ አመሰተርዳም በተልእኮ ተማርን እያሉ የህግ ማስትሬት ዲግሪ ይዘዉ ብቅ ይሉና የእደትና የደሞዝ ጭማሪ ይጠይቃሉ። የሰራተኛ አስተዳደር ባለሙያዎችም የት/ርቱን ማስራጃ አቻ ግምት ለማስሰጠት ወደ ት/ት ሚኒሰቴር ይወስዱና ለሚመለከተዉ ሰራተኛ ያቀርባሉ። ሰራተኛዉም በደንቡ መሰረት አቻ ግመታዉን ሰርቶ ደብዳቤ ይሰጣል በዚያ መሰረት ደሞዝ ጭማሪ ይደረጋል።

አንድ ቀን የአንድ ታጋይ የማስትሬት ዲግሪ ማስረጃ ለሰራተኛ አሰተዳደር ባለሙያ ተላከ። አቻ ግምት ተገምቶ እድገቱ እንዲፈፀም የሚል የተመራበት። የሰራተኛ አስተዳደር ባለሙያም የት/ት ማስረጃዉን ተቀብሎ የአመልካቿን ፋይል ቢያገላብጥ የመጀመሪያ ዲግሪ ማስረጃ ያጣና ወደ ባለ ጉዳይዋ ይደውልና የመጀመሪያ ዲግሪ ማስረጃ ስለሌ አቻ ግምት መስጠት አይቻልም ይላታል። ሴትየዋም ይሄ ከውጭ አገር የተገኘ ት/ት ነዉ ወስደህ ንገራቸዉ ብላ ትእዛዝ ብጤ ታስተላልፋለች። የሰራተኛ አስተዳደር ባለሙያም ከምጨቃጨቅ ብሎ ወደ ት/ት ሚንስቴር ይዞት ቢሄድም እንደማይሆን የሚገልፅ ደብዳቤ ተፅፎ ይሰጠዉና እርሱም አምጥቶ ለባለ ጉዳይዋ ይነግራታል።ሴትየዋም ተቆጥታ ትሄድና ለስዩም ትነግረዋለች ስዩምም የወቅቱ ት/ት ሚኒስቴር ለወ/ሮ ገነት ዘዉዴ ደዉሎ በልዩ ሁኔታ እንዲታይ ቢላት አቻ ግምቱ በገነት ዘዉዴ ፊርማ ታጅቦ ከሰራተኛ አስተዳደር ባለሙያ ቢሮ መጣና ሴትየዋ እድገቱን እንድታገኝ ሆነ። ምንም እንኳ ከመጀመሪያ ዲግሪ በፊት ለተገኘ ማስትሬት ዲግሪ እዉቅና የማይሰጥ ቢሆንም ለታጋዮቹ ግን የሚከለከል አይደለም።ለእነርሱ ሁሉም ነገር በልዩ ሁኔታ ይፈፀማል። በጦር ሜዳ ያሳለፍት ግዜ በሙሉ ቀጥታ አግባብ እንዳለዉ የሥራ ልምድ እየተያዘ ከማንኛዉም ኢትዮጵያዊ በተለየ ሁኔታ እደገትና ሹመት እየተሰጣቸዉ ይገኛል።

አምሰተርዳም ከሚባል አገር የህግ ማስትሬት ዲግሪ ያልተገዛለት የወያኔ ባለስልጣን በቁጥር ሲሆን ለዚህም የሚከፈለዉ ከኢትዮጵያ መንግስት በጀት ወጭ እየተደረገ ነዉ። 12ኛ ክፍል ማጠናቀቃቸዉ በዉል ሳይረጋገጥ በዓለም አቀፍ ህግ ማስትሬት ዲግሪ በተልእኮ ተምሮ ማምጣትና እደገትና ሹመት መጠየቅ የተለመደ ተግባር ነዉ። በእርሻ ሙያ ዲፕሎማ ተመርቀው ካመስተርዳም ባለማቀፍ ህግ ማስትሬት ዲግሪ የጨበጡ ካድሬዎች ብዙ ናቸዉ።

የአንድ መ/ቤት ሠራተኞች የርስ በርስ ግኑኝነት በመተማመን ላይ የተመሰረተ ቢሆን ለመ/ቤቱ የሥራ ስኬት ወሳኝ ሚና ይኖረዋል። በውጭ ጉዳይ ሰራተኞች መካከል ግን ምንም ዓይነት መተማመንና ግልፅነት የሚባል ነገር የለም። ይህን ነገር በምሳሌ ባሳያችሁ ይቀላል። አንድ ቀን እንዲህ ሆነ ከመ/ቤቱ ክበብ ውስጥ በረፍት ሰዓት ሻይ ቡና እያልን ስለ መሬት መሸጥ አለመሸጥ ሁኔታ እናወራለን በዚያች ሰዓት በዚያች ጠረጴዛ ዙሪያ የነበርን ሁላችንም የመሬት ባለቤቱ መብት ያለምንም መሸራረፍ መከበር አለበት የሚል አቋም ነበረን። በዚህ መካከል እኛ ወደነበርንበት አንድ ካድሬ ቢጤ የትግራይ ሰዉ ሲመጣ ያየ አንዱ ድመፁን ከፍ አድርጎና አዲስ መጪዉ እንዲሰማዉ አድርጎ “መሬት ይሸጥ ይለወጥ የሚሉ ጥገኞች ብቻ ሳይሆኑ የቀድሞ ስርዓት ናፋቂዎች ናቸዉ “ብሎ ሲናገር ሁላችንም ሳቃችንን መቋቋም አቃተን። የመጣዉም ካድሬ ብጤ ‘what is so funny guys “ቢለን እኛም “Nothing sir” ብለን አደበስብሰን አልፈን ሌላ ወሬ ጀመርን። እንግዲህ የህዉሃት ካድሬዎች/ደጋፊዎች ነን ከሚሉ ሰራተኞች ጋር የነበርን ግኑኝነት ይህን ይመስል ነበር። ማንኛዉንም አገርን የተመለከተ ጉዳይ በነፃነት ቁጭ ብለን ሳንነጋገር እነረሱም እኛን ለማዳመጥና ስሜታችንን ለመረዳት ፍላጎት ሳያሳዩ እንዲሁ ሆድና ጀርባ ሆነን ግዜዉ ያልፍ ነበር። የሆነ ሆኖ ቅንጅት የመጣ ግዜ የተወሰነዉ ሰራተኛ ሰሜቱን መደበቅ ባለመቻሉ በተወሰነ ደረጃ ፍላጎቱን በመግለፅ ለቅንጅት ያለዉንም ድጋፍ በተለያየ መንገድ በማሳየቱ ከመ/ቤቱ የመባረር እጣ ገጠመዉ።

### ቅንጅት ያመጣው ጣጣ

**ቅንጅት** መንፈስ ነበር። የነጻነት የእኩልነት የዴሞክራሲ እና የፍትህ መንፈስ።ያ የነጻነት መንፈስ በነፍሰ ገዳዮች ከመዳፈኑ በፊት አብዛኛው የውጭ ጉዳይ ሰራተኛ የቅንጅት ደጋፊ ሁኖ ነበር።ግና ምን ያደርጋል ከውስጥም ከውጭም ጠላቶች ተነሱና ያንን በጎ መንፈስ አዳፈኑት። ነፃነት እፈልጋለሁ ብሎ የተነሳዉን ኢትዮጵያዊም በሞት ቀጡት። ከግድያው በኋላ የውጭ ጉዳይ ሰራተኞች ስብሰባ ተጠሩና መንግስት **ሰላም ለማስከበር** ሲል በሰልፈኞቹ ላይ የወሰደው እርምጃ ትክክል ነው የሚል አቋም እንዲይዙ ተነገራቸው። ከመ/ቤቱ ሰራተኞች መካከል የህ.ወ.ሃ.ት አባላትና ደጋፊዎቻቸዉ ብቻ ይህን ሃሳብ አድንቀው አሺ ብለው ተቀበሉ።የሌላው ብሄረሰብ አባላት ግማሾቹ አጉረመረሙ ገሚሶቹ ዝምታን መረጡ።

ህጻናት ወንዶች ሴቶች አና አዛውንቶች ደረትና ራሳቸው ላይ በጥይት ተመተው እንዲገደሉ ሲደረግ ምን ብለን ነው ይህን ትክክል ነው ብለን አቋም የምንይዘው ብለው አጉረምርመዋል የተባሉ ከ35 አስከ 40 የሚደርሱ ሰራተኞች እንዲባረሩ ተደረገ። የስራ ልምዳቸውንም የሚገልጽ ማስረጃ እንዳያገኙ ተከለከሉ።በዚህም ላካበቱት ሙያ የሚመጥን ሥራ ማግኘት አቅቷቸዉ ስራ ፈት ሆነዉ ቀሩ። ከእነዚህ መካከልም ሁለቱ ሞቱ።አንዱ መለሰ ተ/ማሪያም የሚባል ሲሆን በብስጭት አሰላ ሂዶ ከናቱ ቤት ውስጥ ራሱን ሰቅሎ ህይወቱን ሲያጠፋ ሌላው አክሎግ እምሩ የሚባለው ደግሞ ከስራ ከተባረረ በኋላ እቤቱ ውስጥ ሙቶ ተገኝቷል። በወቅቱ ዝም ያሉት የሌሎች ብሄር አባላትና ወሬ በማቀበል የተባበሩት የትግራይ ካድሬዎች በየኢምባሲው ሹመት አገኙ።

ዛሬ በየኢምባሲዉ ተኮልኩለዉ የምናያቸዉ ዲፕሎማት ተብየዎች ሁለት ገፅታ ያላቸዉ ናቸዉ። አንደኛዉ የወቅቱን ግድያ አይተዉና አዝነዉ ግን ደግሞ ምንም ማድረግ አንችልም ብለዉ ዝም ያሉ ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ ከላይ የጠቀስናቸዉን የስራ ጓዶቻቸዉን ለማስባረር ወሬ በማቀበል የተባበሩና ወያኔ የፈፀመዉን ግድያ አግባብ ነዉ ብለዉ የሚያምኑ ፍፁም ካድሬዎች ናቸዉ።

### የዲፕሎማቶች ስደትና የስዩም አስተያየት

በዲፕሎማቶች ስደት ኢትዮጵያ ከአገራቱ ሁሉ ቀዳሚውን ስፍራ ትይዛለች። እንደ ስዩም ግንዛቤ ዲፕሎማቶች የሚሰደዱት የኢኮኖሚ ጥቅም ፍለጋ ነው። የውጭ አገር በርገር ስቧቸው።ይህ ሰው ሌሎቹን የሚገመግመው በራሱ ውስጥ እያያቸው ስለሆነ አልፈርድበትም። እነዚህ የህወሃት ታጋዮች ለሚበላና ለሚጠጣ ሙት ነገር ሲሉ ከምድር በታች የማይፈጽሙት ምንም የወንጀል አይነት አይኖርም። ሌላውም ልክ እንደ እነርሱ ይመስላቸዋል። ስለዚህም ዲፕሎማቶቹ ተከብረው የሚኖሩበትን አገር ጥለው የሚሰደዱት የሚበላና የሚጠጣ ነገር ፍለጋ ነው ይለናል ስዩም መስፍን።

እውነቱ ግን ዲፕሎማቶቹ ተከብረው ከሚኖሩበት አገር ይልቅ ስደት መርጠው በሰው አገር እጅግ አስቸጋሪና አስልቺ የሆነ ስራ እየሰሩ ለመኖር የሚመርጡበት ዋናው ምክንያት በገዛ አገራቸው ስደተኛና መጻተኛ ሁነው ከመኖር ይልቅ አንደኛውን የሰው አገር ስደት ይሻላል ብለው ነው እንጂ ስዩም እንደሚለዉ የሜሪካና የአውሮፓ በርገር ስቧቸው አይደለም። በተለያየ ጊዜ የተሰደዱ ዲፕሎማቶች የስደታቸውን ምክንያት አብራርተው ጽፈዋል።

ዲፕሎማቶቹ ብዙ ገንዘብ ወጪ ተደርጎባቸዉ ሳይማር ያስተማራቸዉን ወገናቸዉን እንዲያገለግሉ ተብለዉ በተለያዩ አገራት ኢትዮጵያን ወክለዉ ይላካሉ።ሁሉም ዲፕሎማት አገሩን የሚወድ ለአገሩም አንዳች በጎ ነገር ለማድረግ የሚመኝና የሚፈልግ ነበር። ሆኖም ግን ይህን በጎ ምኞቱን በተግባር ለማዋል በየኢምባሲዉ የተጎለቱ የህዉሃት ካድሬዎች ከ እነርሱ ፍላጎት ውጭ ምንም ነገር እንዲሰራ ስለማይፈቅዱለት በጎ ምኞቱ ከንቱ ሆኖ ይቀራል። ደፍረዉ የካድሬዎችን ጣልቃ ገብነት የሚቃወሙ ካሉም ዲፕሎማቲክ ፓስፖርታቸዉን እነዲያስረክቡ ይታዘዛሉ እመቢ ካሉም እንዲሰረዝ ላሉበት አገር ባለስልጣናት ያሳዉቁና ዲፕሎማቶቹን ያለ መታወቂያ ባዶአቸዉን ያስቀሩዋቸዋል። ያለ መታወቂያ መገኘት ደግሞ ዲፕሎማቶችን ወንጀለኛ ስለሚያስብል ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ያን አገር ለቀዉ መሰደድ ወይም ደግሞ የፖለቲካ ጥገኝነት መጠየቅ ግድ ይሆንባቸዋል።

በዚህ ሁኔታ ተወልደዉ ያደጉበትን አገር ጥለዉና ላለመመለስ ወስነዉ የተሰደዱ ዲፕሎማቶች ቁጥር ብዙ ነዉ። እኔ ባለኝ መረጃ መሠረት የማዉቃቸዉን ሰደተኞች ስም ከዚህ ፅሁፍ በስተመጨረሻ አቀርቤአለሁ።

### *ማዳም ፈለግ*

ማዳም ፈለግ የስዩም ሚስት ነች።ኤርትራዊ ነች ብለው የነገሩኝ አሉ እኔ ግን መረጃ የለኝም። ይህች ሴት ኤርትራዊም ትሁን ኢትዮጵያዊ ውጭ ጉዳይ ቢሮ ስትመላለስ ኣይቻታለሁ። ወ/ሮ ፈለግ ጸጉሯን ፍርዝ አድርጋና ወደ ኋላ ለቃው ካባ ደርባ ፈረሳይኛ ቋንቋ ከምንማርበት ክፍል ስትገባ ሁላችንም ተደምመን አየናት። ይህች ደግሞ ማነች ብለን መጠያየቅ ጀመርን።

አንዱ ድምጹን ዝቅ አድርጎ ‘የክቡርነታቸው ጸሃፊ ነች መሰለኝ’ አለ። ሌላኛው ተቀብሎ “‘ኖ” እኔ ጸሃፊዎቹን አውቃቸዋለሁ ይህችን ግን አይቼያት አላውቅም’ አለ። ‘ምናልባት ከውጭ ከተመለሱት መካከል አንዷ ትሆናለች አለ” ሌላው ።አንዱ በፍጥነት “እናንተ አግብታ ይሆን እንዴ” ሲል ጠየቀ፤ ይህን ሲሰማ የነበረ ከፊት ለፊታችን የነበረ አንድ ሌላ ተማሪ ትንሽ ወረቀት ጽፎ ላከልን። ”ሴትየዋ የክቡርነታቸው ሚሽት ነች” የሚል።የሰው ሚስት በመሆኗ የተናደደው ግለሰብ እንዲህ አለ “ለውጭ ጉዳይ ሰራተኞች በተዘጋጀ ት/ት እርሷ ምን ቤት ነች ታደያ ? እንደዚያ ከሆነ ደግሞ ሁሉም ሚስቱን አምጥቶ በነጻ ማስተማር አለበት” ሲል አጉረመርመ። ሌላው ደግሞ “አንተ ሚስት የለህ ምን እንዲህ አደረገህ” ሲል አስተማሪው ስም መጣራት ጀመረ። ማዳም ፈለግ! እዚህ ነኝ የሚል ድምጽ ወደተሰማበት ሁላችንም አፈጠጥን። ”የክቡርነታቸውን” ሚስት ለማየት። የሚንስትር ሚስት መሆን መልካም ነገር ነው። ይኅው የቤት እመቤቷ ወ/ሮ ፈለግ እቤት ቁጭ ማለት ቢደብራት ልትደበር እዚህ ከእኛ ክፍል ተገኘችና እኛም አወቅናት።

የእቃ ግዚ ሰራተኞች እንደነገሩኝ ከሆነ ማዳም ፈለግ በማስታወቂያ ያየችውንና ቀልቧ የወደደውን ማንኛውንም እቃ ቀጥታ ደውላ ባስችኳይ እንዲገዛልኝ ብላ ማዘዝ ትችላለች።ሁል ግዜ የእርሷ እቃ ለምን አስቸኳይ እንደሚባል ነው ያማይገባኝ ይላል የእቃ ግዢው ሰራተኛ ወዳጄ። እርሷ ጠይቃ ሳይገዛ የቀረ የእቃ አይነት የለም። የምትኖርበት ቤት የመንግስት ስለሆነ ሁሉም አስፈላጊ ነገር የሚሟላው በመ/ቤቱ ወጭ ነው።ግብር ከፋዩ ቁሞ ይሂድ እንጂ በየ አውደዓመቱ የቤት እቃ ለመቀያየር ማዳም ፈለግ ባለሙያ ነች።

ባለቤቷ አራት አዳዲስ መኪናዎችን በስሙ ይዟል። ሁለቱ የራሱ ሲሆን አንዱ የማዳም ፈለግ አንዱ ደግሞ የልጆች የሸንኩርትና የበርበሬ መግዣ ነው።አራቱም መኪናዎች የየራሳቸው ሾፌሮች አሉዋቸው።እነዚህ መኪኖች ምንም አይነት አስቸኳይ የአገሪቷ ስራ ቢኖርም አይንቀሳቀሱም። ምናልባት እቴ እሜቴ ሽርሽር መውጣት ቢፈልጉና መኪና የለም ቢባሉ የሚመጣውን ጣጣ ማንም ማየት ስለማይፈልግ መኪናዎቹ ሁሌም ዝግጁ ሁነው ነቅተዉ ይጠብቃሉ እንጂ ለመንግስት ስራ አይውሉም።

ክፍል 4 በሚቀጥለው ሳምንት ይቀርባል

## ወያኔ አዳዲስ የጦር መሳሪያዎችን . . . ከገጽ 1 የዞረ

የወያኔው አምባገነናዊ አገዛዝ በሃገሪቱ በሚሊየኖች የሚቆጠሩ የህብረተሰብ ክፍሎች በርሃብ አለንጋ እየተገረፉ ባሉበት ሁኔታ ከጊዜ ወደ ጊዜ ከፍተኛ የሆነ የውጭ ምንዛሪን በማውጣት የጦር መሳሪያ የመግዛቱን እንዲሁም የጦር ሰራዊቱንም ቁጥር ከፍ በማድረግ በተለይም የትግራይን ክልል ከሃገሪቱ ክልሎች በተለየ መልኩ የጦር ቀጠና እያደረጋት እንደሚገኝ የዘገቡት እነኚህ የውስጥ አዋቂ ምንጮቻችን፡ ቀደም ብሎ ወያኔ ወደ ስልጣን ወምበር ከመምጣቱ በፊት በሰሜን ጎንደር የወልቃይት ጠገዴ መሬት የነበሩትንና ባሁኑ ሰዓት የምእራብ ትግራይ አካል የሆኑትን የዳንሻ፤ ባከር፤ ሁመራ፤ በረከት/ሉግዲ ተራራ፤ እና ሌሎችንም አካባቢዎች ያሉ የጦር ሰፈሮቹን በከፍተኛ የሰራዊት ቁጥርና በአዳዲስ የጦር መሳሪያም የማጨናነቁ ተግባር ባሁኑ ሰዓት ባካባቢው አገዛዙን ከፍተኛ ስጋት ላይ የጣለና ፈታኝ ሁኔታ መኖሩን የሚያመለክት ነው ሲሉ ገልጸዋል።

መለስ ዜናዊ በየአቅጣጫው የተነሳበትን የውስጥ ተቃውሞ ለማፈን አዳዲስ የጦር መሳሪያዎችን እየሸመተና ወደ ሰሜን እየላከ እንደሚገኝ ተደጋግሞ የተዘገበ ሲሆን፣ ጉዳዩን በቅርበት የሚከታተሉ ወገኖች እንደሚሉት ግን ወያኔ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የጦር ሰራዊቱን ወደ ትግራይና ጎንደር የጠረፍ ከተሞች የሚያስጠጋው በትግራይ ውስጥ እየታየ የመጣው ህዝባዊ ለውጥ በመከላከያ ሰራዊቱ ውስጥ ገብቶ ሰራዊቱን እንዳይከፍለው በመስጋት የመከላከል እርምጃ ለመውሰድ ነው ሲሉ የአምባገነኑ መለስ ዜናዊ አገዛዝ ሰሞኑን በፓርላማ ተገኝቶ በአገር ውስጥ ያሉ ሀይሎች ትርምስ ለመፍጠር እየሰሩ ናቸው ብሎ መናገሩ ከዚሁ ጋር ተያይዞ መታየት እንዳለበት ያሰምሩበታል።

## የቀድሞው የባንድ ኤይድ ዳይሬክተር ህወሀት . . . ከገጽ 1 የዞረ

ጽሁፉ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ባወጣው ዘገባ በሲአይ ኤ የ1985 ሪፖርት የተወሰነ ገንዘብ ለጦር መሳሪያ ግዢ እንደዋለ መግለጹ ተጠቅሶ የጆህን ጄምስ ምስክርነት በወቅቱ ስለነበረው የርዳታ ገንዘብ ለጦር ግዢ የመዋል ሚስጥር እውነትነት የበለጠ አረጋግጦልናል ብሏል። በመቀጠልም ቦብ ጊልዶፍ ይህን የኢዮጵያ አገዛዝ ለፍርድ ያቅርብ አያቅርብ ወደፊት የምናየው ይሆናል በሚል ጽሁፉን አጠቃልሏል፡፡

መለስ ዜናዊ እንዲህ አይነቱ ውንጀላ ምርጫ ስለደረሰ የሚደረግ የስም ማጥፋት ዘመቻ ነው በሚል ምርጫው እውነተኛ ፉክክር ያለበት ለማስመሰል ቢጥርም፣ የአለማቀፉ ማህረሰብ ግን ለመለስ ጩሀት ቦታ ሳይሰጠው ጉዳዩ እንዲጣራና ተጠያቂ የሚሆኑ አካላትም ለፍርድ እንዲቀርቡ በመወትወት ላይ ነው።

በተያያዘ ዜናም አምባገነኑ መለስ ዜናዊ የፊታችን ሳምንት ወደ ለንደን እንደሚጓዝ ለማወቅ ተችሎአል። ለንደን በሚቆይበት ጊዜም ከኢትዮጵያውያን ከፍተኛ ተቃውሞ ይጠብቀዋል ተብሎ ይጠበቃል።

## ሂዩማን ራይትስ ወች በኢትዮጵያ ያለው . . . ከገጽ 1 የዞረ

የህዝቦችን ነጻነትና የዜጎቹን ነጻ እንቅስቃሴ በጂጉ የሚያግዱ ህጎችን ማውጣቱን፤ በነኝህም ምክንያቶች በጣም ከፍተኛ የሚባል የሰባዊ መብቶች ጥሰትና ረገጣ መከናወኑን ጠቅሷል።

ሪፖርቱ ባሁኑ ሰአት በኢትዮጵያ በትክክል እየሆነና በግልጽም እየታየ ያለው ዜጎች በነጻነት መናገር ያለመቻል፤ ራሳቸውን በማደራጀት በፖለቲካ እንቅስቃሴዎች እንዳይሳተፉ የማድረግ፤ እንዲሁም ሰላማዊ በሆነ መንገድ ለአገዛዙ ያላቸውን ተቃውሞ መግለጽ ያለመቻል መሆናቸውን አያያዞ ጠቅሷል። እውነታው ይህ ሆኖ ሳለ አገዛዙ በሃገሪቱ ዲሞክራሲያዊነትን እያሰፈነ እንደሆነ ለመከራከር መሞከሩ የማያስኬድ እንደሆነ፤ ለዚህም ዋነኛ ምክንያቶቹ ቀደም ብሎ የተገለጹት ከሰባዊ መብት ረገጣ እስከ ንጹሃን ዜጎች ግድያ ችግሮች ያሉበት በመሆኑ ነው ብሏል።

ሂይማን ራይትስ ዋች ይህን ሪፖርት ይፋ ያደረገው ከፍተኛና ጥንቃቄ የተሞላበትን እንደፈረንጆቹ አቆጣጠር የ2009 ዓምን ጥናት መሰረት በማድረግ መሆኑን፤ በተለያዩ የሃገሪቱ ክልሎች ከ50 በላይ በሚሆኑ ቀበሌዎች የሚገኙ ግለሰቦችን ቃለ መጠይቅ ማድረጉንና ከ12 ዓመታት በላይ የሆኑ የሂዩማን ራይትስ ዋች ጥናቶችን ማገናዘቡን አውስቶ ይህንም መሰረት በማድረግ በአጠቃላይ በሃገሪቱ የፖለቲካው ሂደት ምን እንደሚመስልና ምርጫ 2002ም ምን ሊመስል እንደሚችል ጠቁሟል።

ሪፖርቱ በማጠቃለያው በኢትዮጵያ ያለው አሳሳቢ ሁኔታ መፍትሄ ያገኝ ዘንድ ባስቸኳይ ሊወሰዱ ይገባቸዋል ብሎ ያመነባቸውን ነጥቦች በዝርዝር አቅርቧል። በዚህም መሰረት የኢትዮጵያው አገዛዝ ባስቸኳይ ግልጽ በሆነ ቋንቋ በህዝቦች ላይ እያደረገ ያለውን ማዋከብና የመብቶች ጥሰት ባስቸኳይ እንዲያቆምና ይህንም እንዲያሳውቅ፤ ከተቃዋሚ ፓርቲዎች የቀረቡ አቤቱታዎችን በተገቢው መንገድ ተመልክቶ መፍትሄ እንዲፈልግ፤ ያለአግባብ በፖለቲካ አመለካከታቸው የታሰሩ ንጹሃን ዜጎችን እንዲለቅ እንዲሁም ወ/ት ብርቱካን ሚዴቅሳን ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ከእስር እንዲፈታ ሲል ጠይቋል። “ተገቢ ያልሆኑና የህዝቦችን ነጻ እንቅስቃሴ አፋኝ የሆኑ ህጎችን እንዲያሻሽል፣ በ2002 ምርጫ ዙሪያ ፍትሃዊ የሆነ ምርጫ የሚካሄድበትን ፣ ኢትዮጵያዊያን ያለምንም ገደብ መረጃ ከዓለም አቀፍ ነጻ ሚዲያዎች እንዲያገኙ፣ ነጻና ገለልተኛ የሰብአዊ መብት ተሟጋች ተቋማት ነጻ የሆነ የማጣራትን ስራ እንዲያከናውኑ እንዲሁም በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ዜና ማሰራጫዎችን ከማዋከብ ለመቆጠቡ ገደብ የሌለዉ ዋስትና እንዲሰጥ” ሲል አሳስቦአል።

ድርጅቱ የምእራብ አገሮች በኢትዮጵያ ውስጥ ነጻና ፍትሀዊ ምርጫ እንዲደረግ ጫና ማድረግ አለባቸው ሲልም ገልጿል። ኢዩማን ራይትስ ወች ኢትዮጵያን አስመልክቶ ያወጣው ሪፖርት ቢቢሲን ጨምሮ በተለያዩ አለማቀፍ የመገናኛ ብዙሀን የተዘገበ ሲሆን፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የአለማቀፍ የመገናኛ ብዙሀን የወያኔን አገዛዝ መመርመር መጀመራቸው ለአለፉት አምስት አመታት ከፍተኛ ትግል ሲያደርጉ የነበሩ በውጭ ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን ከፍተኛ ድልና ማበረታቻ ሲሆን፣ ለወያኔ ዲፕሎማሲ ደግሞ ከፍተኛ ኪሳራ ነው ተብሎአል። በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ከዚህ በፊት እንዳደረጉት ሁሉ ትግላቸውን አጠንክረው የሚቀጥሉ ከሆነ ፣ እነአሜሪካና የአውሮፓ መንግስታት በኢትዮጵያ ላይ የሚከተሉትን የተዘባ ፖሊሲ ለማስቀየር እንደሚችሉ በድህረገጾች ላይ የሚወጡ አስተያየቶች አመልክተዋል።

## የወ/ት ብርቱካን ሚዴቅሳ የጤና ሁኔታ . . . ከገጽ 1 የዞረ

“እየሆነ ላለው ሁሉ የአይን እማኞች ነን ይህ ቀን አልፎ ከፍትህ አደባባይ ቆመን የምንመሰክርበት ቀን ይመጣ ይሆናል፤ ከምናየው በላይ እጅግ ያበሳጨን ደግሞ የመለስ ዜናዊ አባባል ነው ያሉት የመረጃው ምንጮች፣ ወላጅ እናቷና ልጇ ብቻ እንደሚጠይቋት፡ ቀደም ሲል ትጠይቃት የነበረችው እህቷ እንኳን ብርቱካንን መጠየቅ ከተከለከለች ወራት መቆጠራቸውን እንዲሁም እናቷ ይዘውት የሚሄዱትን ቀለብና ልብስ መያዝ እያቃታቸውና የሚያግዛቸው ሰው እንዳይኖር ተከልክለው የምትችይውን ብቻ ይዘሽ ነይ መባላቸውን ገልጸዋል፡፡ እኒሁ በወህኒ ቤቱ አካባቢ የተገኙት መረጃዎች እንዳረጋገጡት ብርቱካን ህክምና እንድታገኝ ከመጠየቅ ባለፈ ህመሟን ቤተሰቧ እንዲያውቅ ባለመፈለግ ይመስላል ከእናቷ ጋር ስትገናኝ ፍጹም ጤነኛ መስላ እንደምትታይ ገልጸው፣ አሁን ግን ህመሙ ከም ትችለው በላይ ሆኖባት ይመስላል መጋቢት 12/2002 ለእናቷ ለመናገር ስትሞክር የወህኒ ቤቱ ፖሊሶች እየገፈተሩ ወደ ክፍሏ ሲያስገቧት በዚሁ እለት እናትና ልጅ በእንባ ነው የተለያዩት ብለዋል፡፡ ይህም ክፉኛ እንዳሳዘናቸውና እንዲህ አይነቱን አረመኒያዊ ግፍ ከዚህ በላይ አፍነው መያዝ እንዳላስቻላቸው ይናገራሉ፡፡

ግንቦት 7 አሳሳቢ እየሆነ የመጣውን የወ/ት ብርቱካንን የጤና ሁኔታ አስመልክቶ ትናንት ማምሻውን በጽሁፍ በሰጠው መግለጫ፣ ወ/ት ብርቱካን ምንም አይነት ወንጀል ሳትሰራ በአምባገነኖች ትእዛዝ የታሰረች የህሊና እስረኛ መሆኑዋን፣ ወንጀል አለባት ከተባለም ወንጀሉዋ ለእውነት መቆሟ መሆኑን እንዲሁም ተገቢ የሆነ የህክምና እርዳታ እንዳታገኝ መከልከሉዋ በእጅጉ እንዳሳዘነው በመጥቀስ ድርጊቱን በጥብቅ ያወገዘ ሲሆን፣ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የህሊና እስረኛዋ በአስቸኳይ ከእስር የምትለቀቅበትን መንገድ ለማፈላለግ በጋራ መነሳት እንዳለበት አሳስቦአል። ወ/ት ብርቱካን በአምባገነኖች ትእዛዝ ወህኒ እንድትወርድ ከተደረገችበት ጊዜ ጀምሮ፣ ግንቦት7 ድርጊቱን በማውገዝ ተደጋጋሚ መግለጫ ሲያወጣ መቆየቱ ይታወሳል።

## የአማራ ክልል አስተያየት ሰጪዎች ወያኔ . . . ከገጽ 1 የዞረ

የህዝቡ ትግስትም ማለፍ ከሚገባው ገደብ በላይ መሄዱን የሚያሳይ ነው ብለዋል።

ወያኔ በቁጥጥሩ ስር ባለው ዜና ማሰራጫ እንደፈለገው ይናገር እንጂ የወያኔን ውልደትና እድገት እንዲሁም ማንነት አበጥሮ የሚያውቀው ህዝብ ፣ለወያኔ ልመና ፍጹም ጆሮ እንደሌለው፣ ምን ማድረግ እንዳለበትም ሌት ከቀን እየተመካከረና አመቺ ሁኔታንም እየጠበቀ እንደሆነ እኚሁ አስተያየት ሰጪ ተናግረዋል። በመጨረሻም የህዝብን ጩከት የሚሰማ በሌለበ ሃገር፤ ሙስና እጂግ በተስፋፋበትና እንደባህልም እየተወሰደ ባለበት ሁኔታ፤ የህግ የበላይነትን ረግጠውና አፍነው የሚገኙ ባለስልጣናትንና ካድሬዎች ህዝብ ፈቃደኛ ሆኖ ይመርጣቸዋል ተብሎ እንኳን ሊታሰብ ሊታለምም የማይቺል ነው በማለት አስተያየታቸውን አጠቃልለዋል።

የግንቦት ሰባት ንቅናቄ በተደጋጋሚ የወያኔን አገዛዝ በሚገባው ቋንቋ አስገድዶ ስልጣኑን እንዲለቅ ከማድረግ የተሻለ አማራጭ እንደሌለ መግለጹና ለዚህም ኢትዮጵያዊያን ከጎኑ እንዲሰለፉ ጥሪ ማቅረቡ ይታወሳል።

## በርካታ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ውሀ ካዩ . . . ከገጽ 1 የዞረ

ርቀት እየተጓዙ እንደሆኑ በዚህም ምክኒያት የእለት ከእለት ኑሮአቸውም በከፍተኛ ሁኔታ ፈተና ላይ እየወደቀ መሆኑን በምሬት መናገራቸውን ዘጋቢያችን ገልጿል።

የግንቦት ሰባት ዘጋቢ ካነጋገራቸው የህብረተሰብ ክፍሎች አብዛኞቹ በሰጡት አስተያየት ወያኔ በዜና ማሰራጫው ከ66 በመቶ በላይ በሃገራችን የንጹህ ውሃ አቅርቦት አለን እያለ አሰልቺ የሆነ ልፍለፋውን እያሰማ ባለበትና በዓለም አቀፍም ደረጃ 18ኛው የንጹህ ውሃ መጠጥ ቀን እየተከበረ ባለበት ወቅት እንዲህ አይነት ቺግር በሃገሪቱ ርእሰ ከተማ እየታየ መሆኑ የዚህን አገዛዝ መሳቂያነት የሚያረጋግጥልን ነው ብለዋል፡፡

የአዲስ አበባ ነዋሪ በውሀ እጥረት በተደጋጋሚ ሲጠቃ መቆየቱ የሚታወቅ ሲሆን፣ እንደሰሞኑ ግን ሆኖ እንደማያውቅ ነዋሪዎች ይናገራሉ። ችግሮች ሲፈጠሩ በቀልድ ማሳለፍ የሚመርጠው የኢትዮጵያ ህዝብ፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተደጋጋሚ የሚታየውን የውሀ ችግር ለመተቸት “ውሀችን ተጠልፎ ግልገል ጊቤን ሊያበራ ሄዷል” እያለ እንደሚቀልድ ታውቋል።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

**በ 7530 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ** እና **በ 9610 KHZ በ 31 ሜትር ባንድ** ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን g7radio@ginbot7.org ወይም በስልክ ቁጥር 0044- 203-286- 9661